የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሳኛ ዓመት ቁጥር ፪
አዲስ አበባ ጥቅምት ፭፱ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No.2
ADDIS ABABA 9th November, 2023

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፺፱/፪ሺ፲፭

የሕዝብን ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅ የወጣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፮/፪ሺ፲፭ን ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ ገጽ ……..…፲፭ሺ፪፻፵፭

Content

Proclamation No. 1299/2023

A State of Emergency Proclamation Enacted to Protect Public Peace and Security No. 6/2023 Ratification Proclamation …….....Page 15245

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፺፱/፪ሺ፲፭

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሕዝብን ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅ ያወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፮/፪ሺ፲፭ን ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

የሕዝብን ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅ የወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፮/፪ሺ፲፭ ሐምሌ ፳፭ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም በሚኒስትሮች ምክር ቤት የታወጀ በመሆኑ፤

ይሔው በሚኒስትሮች ምክር ቤት የታወጀው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ ፶፫ ንዑስ አንቀፅ (፪)(ለ) መሠረት በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መቅረብ ያለበት በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትም ነሐሴ ፮ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም ባካሄደው ፩ኛ አስቸኳይ ስብሰባ የመረመረውና በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ ፶፫ (፫) መሠረት ያፀደቀው ስለሆነ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ ፶፫ ንዑስ አንቀፅ (፪)(ለ) እና አንቀፅ ፶፭ ንዑስ አንቀፅ (፰) መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

PROCLAMATION NO. 1299/2023

THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA COUNCIL OF MINISTERS STATE OF EMERGENCY PROCLAMATION ENACTED TO PROTECT PUBLIC PEACE AND SECURITY PROCLAMATION NO. 6/2023, RATIFICATION PROCLAMATION

WHEREAS, the Council of Ministers has approved on 4th day of August, 2023 A State of Emergency Proclamation to Protect Public Peace and Security Proclamation No. 6/2023;

WHEREAS, based on Article 93 Sub-Article (2) (b) of the Constitution, the State of Emergency Proclamation decreed by the Council of Ministers shall be presented to the House of Peoples' Representatives within fifteen days;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives has ratified this Proclamation based on Article 93 Sub-Article (3) of the Constitution, on its 1st extra ordinary session held on the 14th day of August, 2023;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 93 Sub-Article (2)(a) and Article 55 Sub-Article (8) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የሕዝብን ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅ የወጣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፮/፪ሺ፲፭ን ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፺፱/፪ሺ፲፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

1. Short Title

This Proclamation may be cited as "A State of Emergency Proclamation Enacted to Protect Public Peace and Security No. 6/2023 Ratification Proclamation No. 1299/2023."

፪. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ስለማፅደቅ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሐምሌ ፳፰ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም ያወጀው "የሕዝብን ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅ የወጣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፮/፪ሺ፲፭" በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

2. Ratification of the Proclamation

"A State of Emergency Proclamation to Protect Public Peace and Security No. 6/2023" Enacted by the Council of Ministers on 4th day of August, 2023, is ratified by this Proclamation.

፫. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ

፩/ የሕዝብን ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅ የወጣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪/ መርማሪ ቦርዱ ሰባት አባላት የሚኖሩት ሲሆን፣ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላትና ከሕግ ባለሙያዎች የተውጣጡ ሆነው በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሰየማሉ፡፡

፫/ ቦርዱ ሰብሳቢና ም/ሰብሳቢ የሚኖሩት ሆኖ ይዋቀራል፡፡

፬/ ቦርዱ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ ፺፫ ንዑስ አንቀፅ (፮) ላይ የተመለከቱት ሥልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

3. State of Emergency Inquiry Board

1/ State of Emergency Inquiry Board for the State of Emergency Proclamation Enacted to Protect Public Peace and Security is hereby established.

2/ The Inquiry Board shall comprise seven members to be chosen and assigned by the House from among its members and from legal experts.

3/ The Board may compose a chairperson and a deputy chairperson.

4/ The Board shall have power and responsibilities indicated on Article 93 Sub-Article (6) of the Constitution.

፬. የቦርዱ ሰብሳቢ ሥልጣን እና ተግባር

፩/ ቦርዱን ይመራል፡፡

፪/ አጠቃላይ የቦርዱን የሥራ እንቅስቃሴ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፡፡

፫/ የቦርዱን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ያስተዳድራል፡፡

፬/ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ማንኛውም ግንኙነት ቦርዱን ይወክላል፡፡

4. Power and Responsibilities of the Chairperson of the Board

1/ Lead the Board.

2/ Shall lead and control the activity of the Board.

3/ Shall administer the supporting employees of the Board.

4/ Represent the Board in all dealings with third parties.

፭. <u>የቦርዱ ምክትል ሰብሳቢ ሥልጣን እና ተግባር</u>

፩/ የቦርዱን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀትና በመምራት ሰብሳቢውን ይረዳል፡፡

፪/ ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ለሰብሳቢው የተሰጡ ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

፫/ በሰብሳቢው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

5. <u>Power and Responsibilities of the Deputy Chairperson of the Board</u>

1/ Assist the chairperson by planning, organizing and directing the Boards activity.

2/ Perform the activities of the chairperson in his absence.

3/ Perform the activities assigned by the chairperson.

፮. <u>የቦርዱ ጽህፈት ቤት</u>

የቦርዱ ዋና ጽህፈት ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶችን በሌሎች ቦታዎች ሊከፍት ይችላል፡፡

6. <u>The Office of the Board</u>

The Boards Head Office shall be in Addis Ababa and may have branch office elsewhere in the country as may be necessary.

፯. <u>በጀት እና የሰው ኃይል</u>

ለቦርዱ ሥራ አስፈላጊ የሆነው የሰው ኃይል፣ በጀት እና ጽህፈት ቤት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚሟላ ይሆናል።

7. <u>Budget and Human Resource</u>

Human resource, budget and office which are important for the task of the Board shall be fulfilled by the House of Peoples' Representatives.

፰. <u>የቦርዱ ስብሰባዎች</u>

፩/ ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

፪/ የቦርዱ ውሳኔ በተባበረ ድምፅ ይሆናል፣ በተባበረ ድምጽ መወሰን ባልተቻለ ጊዜ በአብላጫ ድምጽ ይወሰናል፡፡

፫/ ድምጹ እኩል በእኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ያለበት ወገን የያዘው አቋም የቦርዱ ውሳኔ ይሆናል፡፡

፬/ በዚህ አንቀፅ ከንዑስ አንቀፅ (፩) እስከ (፫) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ የውስጥ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

8. <u>Meetings of the Board</u>

1/ There shall be a quorum where more than half of its members are present.

2/ The decisions of the Board shall be passed by consensus, when failing that by majority vote.

3/ In the case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

4/ Without prejudice to Sub-Article (1) to (3) of this Article the Board can have its own internal rules of procedure.

፱. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከታወጀበት ከሐምሌ ፳፰ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም ጀምሮ ለስድስት ወራት የፀና ይሆናል።

9. <u>Effective Date</u>

This State of Emergency Proclamation shall remain in effect for six months starting from 4th day of August, 2023 since the time promulgated by the Council of Ministers.

አዲስ አበባ ጥቅምት ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

ሳህለወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

Done at Addis Ababa, On this 9th day of November, 2023

SAHILEWORK ZEWUDE

PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA